ቁጥር፡ አብክመ/11/251 /መ/ክ-1
ቀን፡ 05/03/2015 ዓ/ም

ለ____________________ ዞን አስተዳደር

__________፤

**ጉዳዩ፡-** **<u>በመስተዳድር ምክር ቤቱ የፀደቀ የኢንቨስትመንት ቦርድ ማቋቋሚያና የአሰራር መወሰኛ ደንብ ስለመላክ፣</u>**

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት መስከረም 24 ቀን 2015 ዓ/ም ባካሄደው 6ኛ ዙር 2ኛ ዓመት የስራ ዘመን 2ኛ አስቸኳይ ስብሰባ " **በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንቨስትመንት ቦርድ ማቋቋሚያና የአሰራር መወሰኛ ደንብ ቁጥር** 205/2015ዓ/ም" ከመረመረ በኋላ አስፈላጊውን ማሻሻያ በማድረግ አፅድቋል፡፡

ስለሆነም ይኸው የፀደቀው ደንብ በመስተዳድር ምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት የታረመና የተስተካከለ በመሆኑ ደንቡ በዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ እስኪወጣ ድረስ በመስተዳድር ምክር ቤቱ ቀርቦ ከፀደቀበት ከነሐሴ 20 ቀን 2014 ዓ/ም ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ይደረግ ዘንድ በውስጡ <u>10 ገፅ</u> እንደያዘ በዚህ ደብዳቤ ሸኝነት የተላከላችሁ መሆኑን እያሳዎቅሁ፣ ይኸው የፀደቀው ደንብ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ የሚመለከታቸው ተቋማት በእናንተ በኩል እንዲያውቁት እንዲደረግና ክትትል እንዲደረግበት አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

<u>ግልባጭ፡</u>
- ለም/ርዕሰ መስተዳድሩ
- ለጽ/ቤቱ ኃላፊ /ያለ አባሪ/
- ለካቢኔ ሴክሬታሪያት ዳይሬክቶሬት
  <u>ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፣</u>
- ለኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ
- ለከተሞችና መሠረተ ልማት ቢሮ
- ለመሬት ቢሮ
- ለማዕድን ቢሮ
- ለገንዘብ ቢሮ
  <u>ባህር ዳር</u>

☎ 0582221437
E-mail anrsprinfo@gmail.com
✉ 312
🖷 +2510582201068
website www.amharareg.gov.et

## ደንብ ቁጥር 205/2015ዓ.ም

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንቨስትመንት ቦርድ ማቋቋሚያ እና የአሰራር መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ፣

የኢንቨስትመንት ጉዳዮች በባህሪያቸው በአንድ ቢሮ የተናጠል ውሳኔ የማይቋጩ እና ለውጤታማነታቸው የሚመለከታቸው ተቋማትን የሚያስተባብርና በበላይነት የሚያስተዳድር ቦርድ ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፣

ኢንቨስትመንት ለክልላዊ ሁለንተናዊ ዘላቂ ልማት ፋይዳው ትልቅ ሲሆን በዚሁ ልክ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ መሆኑን ከማስገንዘብ በላይ መንግስታዊ አስተዳደራዊ ዋስትና የሚሰጥ ተቋም (ቦርድ) ማቋቋም ለኢንቨስተሩ መንግስታዊ ዋስትና መስጠቱን እና ቁርጠኝነትን የሚያረጋግጥ ሆኖ በመገኘቱ፣

በክልሉ ውስጥ የሚደረጉ የኢንቨስትመንት ተግባራት አገራዊ የኢንቨስትመንት ግቦችን ማሳካታቸውን እንዲሁም በሕግ አግባብ መከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር፣ የክትትል፣ የቅሬታ አፈታት ሥርዓት መዘርጋት ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ፤

የኢንቨስትመንት ፍሰት፣ መስፋፋት፣ እና ቆይታን ማሳደግ እንዲቻል ኢንቨስትመንት የሚመራበትን ሥርዓት ይበልጥ ግልጽ፣ ተገማች፣ ታማኝ፣ እናቀልጣፋ እንዲሆን ለማድረግ የኢንቨስትመንት ቦርድ ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ተግባራት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሌሎች ቢሮዎችን የሚመለከቱ ኢንቨስትመንት-ነክ ውሳኔዎችን መወሰን የሚችል ሥልጣን ያለው አካል ማቋቋሙ አስተዳደራዊ አግባብነት ያለው ሆኖ በመገኘቱ፤

የቦርድ መቋቋም የግሉ ሴክተር በክልሉ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ልማት ላይ ድርሻውን ይወጣ ዘንድ አስተዳደራዊ መፍትሄነቱ በመታመኑ፤

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፰ ንዑስ አንቀጽ ፯፣ እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻለው የአስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹/፪ሺ፲፬ ዓ.ም አንቀጽ ፵፬ መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ፣

ይህ ደንብ **"የኢንቨስትመንት ቦርድ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 205/2015 ዓ.ም"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ፣

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. "ቢሮ ወይም ቢሮዎች" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በአዋጅ ቁጥር 280/2014 በቢሮ ደረጃ የተቋቋሙ እና የኢንቨስትመንት ጉዳዮችን ለቦርዱ የሚያቀርቡ ማለት ነው፡፡
2. "ቦርድ" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የተቋቋመው የአብክመ የኢንቨስትመንት ቦርድ ነው፤
3. "ድርጅት" ማለት ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ነው፤
4. "የመንግሥት የልማት ድርጅት" ማለት ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ነው፤
5. "ኢንቨስተር"- "ባለሀብት" ማለት በአማራ ክልል ውስጥ ካፒታል ሥራ ላይ ያዋለ (የሚያውል) የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ባለሀብት ነው፤
6. "ኢንቨስትመንት" ማለት አዲስ ድርጅትን ለማቋቋም፣ ወይም ነባር ድርጅትን ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ለመግዛት፣ ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል በባለሀብት በገንዘብ ወይም በዓይነት ወይም በሁለቱም የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው፤
7. "ካፒታል" ማለት የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ገንዘብ፣ የሚተላለፍ ሰነድ፣ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ መሳሪያ፣ ህንጻ፣ የሥራ ማስኬጃ ጥሬ ገንዘብ፣ የንብረት መብት፣ የአእምሯዊ ንብረት መብት ወይም ሌላ የሚዳሰስ ወይም የማይዳሰስ ሀብት ነው፤

### 3. የተፈጻሚነት ወሰን፣

ይህ ደንብ በውስን እና ለቦርዱ በልዩ ሁኔታ በተሰጡት የኢንቨስትመንት ጉዳዮች እና አሰራሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

### 4. የደንቡ ዓላማ፣

1. በክልሉ በተለዩ እና በተመረጡ የኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ የሚወስን ቦርድ ማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባሩን መወሰን እና በክልሉ የሚደረጉ የኢንቨስትመንት ተግባራት በውጤታማነት የሚተዳደሩበትን እና የሚመሩበትን ሁኔታ ማሳለጥ፣
2. የኢንቨስትመንት አስተዳደሩ ለኢንቨስተሩ አስተማማኝ እና ቀልጣፋ መንግስታዊ አስተዳደራዊ ውሳኔ በመስጠት መንግስታዊ አመኔታን እና ተቀባይነትን ማሳደግ፣

## ክፍል ሁለት

## ስለ ቦርድ መቋቋም፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር

### 5. ስለ ቦርድ መቋቋም

1. የአማራ ክልል ኢንቨስትመንት ቦርድ አንድ የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካል ሆኖ በዚህ ደንብ በክልል፣ በዞን፣ በከተማ እና በወረዳ አስተዳደር ተቋቁሟል።
2. የኢንቨስትመንት አስተዳደሩ እና አሰራሩም በአዋጅ ቁጥር 280/2014 እና በኢፌድሪ ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ በተደነገገው አግባብ የሚመራ ይሆናል።

### 6. በየደረጃው የሚቋቋሙ የቦርዱ አደረጃጀት እና አባላት ስብጥር፣

#### 6.1. የክልል ቦርድ አባላት

1. ቦርዱ በክልል ደረጃ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

ሀ). የክልሉ ርዕሰ- መስተዳደር ..........................................................ሰብሳቢ፤

ለ). የክልሉ ምክትል ርዕሰ- መስተዳደር.........................................አባል፣

ሐ).የኢኮኖሚ ጉዳዮች ክላስተር አስተባባሪ...................................አባል

መ). ከተሞች እና መሰረተ ልማት ቢሮ .......................................አባል

ሠ). መሬት ቢሮ ..............................................................አባል

ረ). ማዕድን ቢሮ .....................................................................አባል

ሰ). ገንዘብ ቢሮ..............................................................አባል

ሸ). ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ..............የቦርዱ አባልና ፀሀፊ ይሆናል።ሌሎች ተቋማት እንደ ኢንቨስትመንቱ ዓይነትና ባህሪ እንዲሁም በቦርዱ ስብሳቢ ውሳኔ በአባልነት ሊሳተፉ ይችላሉ።

### 6.1.1. የክልል ቦርዱ ስልጣንና ተግባር፣

**የክልሉ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤**

1. የዚህን ደንብ አፈፃፀም እና የክልሉን የኢንቨስትመንት በበላይነት ይመራል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤. ኢንቨስትመንትን በሚመለከት ከቦርዱ ስልጣንና ተግባር የሚቀዱ መመሪያዎችን ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣ አተገባበራቸውንም ይከታተላል፤
2. የኢንቨስትመንት መሬት በሚመለከተው አካል ለኢንቨስትመንት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
3. ቦርዱ እንደ አስፈላጊነቱ የኢንቨስትመንት አማካሪ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ኃላፊነታቸውን ይወስናል፣ አባላቱን እና ሰብሳቢዎቻቸውን ይሰይማል፤
4. በክልሉ ለባለሀብቶች የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ዓይነት እና መጠን፣ እንደዚሁም በማበረታቻ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው የኢንቨስትመንት መስኮች የሚለዩበትን መመዘኛ በተመለከተ አግባብነት ላለው የመንግሥት አካል በጥናት ላይ የተመረኮዘ የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብ ያደርጋል፤
5. በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለሚቀርቡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በተለይ የአበባ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣እፀ- ጣዕም፣ቡና፤የመስራች ዘር እና የዘር ብዜት፤ እና ደን ልማት የኢንቨስትመንት አይነቶች ጉዳዩ በሚመለከተው ተቋም/ቢሮ ተገምግሞ ሲቀርብ የሚያስፈልጋቸውን የመሬት መጠን በምደባ ውሳኔ ይሰጣል።

6. በአገልግሎት ኢንቨስትመንት ዘርፍ ከ5000 (ከአምስት ሽህ ካሬ ሜትር) በላይ መሬት ለሚፈልጉ የሆቴል፣ ሎጂ፣ ሪል ስቴት ፕሮጀክቶች በዞንና ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ቦርድ የውሳኔ ሀሳብ ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው ተቋም/ቢሮ ተገምግመው ሲቀርቡ በሚያቀርቡት የፕሮጀክት መነሻ የውሳኔ ሃሳብ መሰረት መሬት በልዩ ሁኔታ በምደባ እንዲያገኙ ልዩ ውሳኔ ይሰጣል፤፡እንዲሁም የጤና፣ ትምህርት፣ ስፖርት ልማት ኢንቨስትመንቶች ከላይ የተገለጸው የካሬ ሜትር መጠኑ ሳይገድባቸው በልዩ ሁኔታ መሬት በምደባ እንዲያገኙ ያደርጋል። አፈጻጸሙንም ይከታተላል።

7. እንደ የዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ነባራዊ ሁኔታና ያላቸውን የመልማት እድል (ፀጋ) መሠረት ያደረገ ልዩ የማበረታቻ ፓኬጅ በማፀደቅ ተቀራራቢ የመልማት እድል በዞኖች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና የገጠር ወረዳዎች መካከል እንዲኖር በትኩረት ይሰራል።

8. በክልሉ ምቹ የኢንቨስትመንት አካባቢያዊ ሁኔታ ለመፍጠርና በዘርፉ የሚታዩትን ተግዳሮቶች ለመፍታት በአመት ሁለት ጊዜ የኢንቨስትመንት ፎረም እንዲካሄድ በጀት እንዲመደብ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን በበላይነት ይመራል።

9. በክልሉ በከፍተኛ አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ የተሰማሩ ፕሮጀክቶች እያጋጠማቸው ያለውን የግብዓት /የግብርና ምርት/ እጥረት ለመፍታት ከአርሶ አደሮች፣ ኢንተርፕራይዞች፣ እና ከባለሀብቶች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ድጋፍ ያደርጋል።

10. ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል መሬት እየተዘጋጀ ለአልሚዎች ስለመተላለፉ፣ በወሰዱት የኢንቨስትመንት ፈቃድና የመሬት ውል መሠረት ወደ ስራ መግባታቸውን ይከተላል፣ ድጋፍ ያደርጋል።

11. ኢንቨስትመንት በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ በቢሮዎች መካከል የሚፈጠር ልዩነት እና ቅሬታ ላይ ገዥ ውሳኔ ይሰጣል፣

12. በከተማ ለአገልግሎት ዘርፍ የሚውሉ ከ1500 በላይ ካሬ ሜትር የሚሆን የመሬት ማስፋፊያ ጥያቄዎች ሲቀርቡ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣

13. ልዩ ክልላዊ ፋይዳ ያላቸው የብረት፣ የክሰል (የኢነርጅ) እና የሲምንቶ ፋብሪካ ኢንቨስትመንቶች ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

14. ቦርዱ የሚያስተላልፋቸውን ውሳኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፣ በማይፈጽሙ አካላት ላይ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።

15. ቦርዱ እንደየሁኔታው ተግባርና ሃላፊነቱን ለመፈጸም በሚያስችለው አግባብ ለተቋማት ውክልና ከተጠሪቂነት ጋር መስጠት ይችላል።

16. በልዩ ሁኔታ በክልል መታዩት ያለባቸው የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች እስ ብሎ ሲያምን ወደ ወረዳ እና ዞን መሄድ ሳያስፈልጋቸው የኢንቨስትመንት ስርጭቱን በማያዛባ እና በሚያስተካክል መንገድ ለዞኖች፣ከተማ አስተዳደሮች ወይም ለወረዳዎች በቀጥታ መልምሎ መላክ ይችላል።

17. በሌሎች ተዛማጅ ክልላዊ ፋይዳ ባላቸው የኢንቨስትመንት ጉዳዮች ላይ አቅጣጫ ወይም ውሳኔ የመስጠት ስልጣን አለው።

18. ከዞን/ሪጆፖሊታንት ከተማ አስተደደሮች ኢንቨስትመንት ቦርድ የሚላኩ የውሳኔ ሀሳቦችን መነሻ በማድረግ አጀንዳው የሚመለከታቸው ቢሮዎች በአዋጅ የተሰጣቸውን ስልጣን መሰረት አድርገው የራሳቸውን አስተያየት ሰጥተው በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ በኩል በአጀንዳነት ለውሳኔ ለክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ ይቀርባል።

## 6.2. የዞን እና ሪጅኦፖሊታን ከተሞች የኢንቨስትመንት ቦርድ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ዝርዝር፣

### 6.2.1. የቦርድ አባላት ስብጥር፣

ሀ. አስተዳዳሪ/ ከንቲባ.................................ሰብሳቢ

ለ. ምክትል አስተዳዳሪ/ ም/ከንቲባ ........................ምክትል ሰብሳቢ

ሐ. ከተማ እና መሰረተ-ልማት መምሪያ.............አባል

መ. መሬት መምሪያ....................................አባል

ሠ. ገንዘብ መምሪያ ...................................አባል

ረ. ማዕድን መምሪያ...................................አባል

ሰ. ኢንዳስትሪ እና ኢንቨስትመንት መምሪያ........አባልና ጸሀፊ ሲሆኑ እንደ ኢንቨስትመንቱ ባህሪ ሌሎች መምሪያዎች አባል እንዲሆኑ በአስተዳዳሪው ወይም ከንቲባው ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

### 6.2.2. የዞን እና ሪጅኦፖሊታን ከተሞች ቦርድ ስልጣንና ተግባር ዝርዝር፣

1. በክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ አቅጣጫ እና ውሳኔ መሰረት ተግባራትን ይፈጽማል።
2. ከወረዳና ከተማ አስተዳደሮች ኢንቨስትመንት ቦርድ ተለይተው እና የውሳኔ አስተያየት ቀርቦባቸው የሚመጡ ኢንቨስትመንቶችን በራሱ በማወዳደር እና በመለየት ጠቃሚና

አስፈላጊነታቸውን ሲያምንበት ከውሳኔ አስተያየት ጋር ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ቢሮዎች ይልካል፡፡

3. በዞኑ ወይም በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ስራዎችን ከሚመለከታቸው መምሪያዎች ጋር በመሆን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
4. ሌሎች በክልሉ ቦርድ ተወስነው የሚሰጡትን ተግባራት ይፈጽማል፡፡

### 6.2.3. የወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ቦርድ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር፣

1. **የቦርድ አባላት ስብጥር፣**

ሀ. አስተዳዳሪ/ ከንቲባ.......................................................ሰብሳቢ

ለ. ምክትል አስተዳዳሪ/ ከንቲባ...........................................ም/ሰብሳቢ

ሐ. ከተማ እና መሰረተ-ልማት ጽ/ቤት...................................አባል

መ. መሬት ጽ/ቤት............................................................አባል

ሠ. ማዕድን ጽ/ቤት..........................................................አባል

ረ. ገንዘብ ጽ/ቤት............................................................አባል

ሰ. ኢንዳስትሪ እና ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት................................አባልና ጸሃፊ

ሲሆኑ እንደ ኢንቨስትመንቱ ባህሪ ሌሎች ጽ/ቤቶች አባል እንዲሆኑ በአስተዳዳሪው/ከንቲባው ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

### 6.2.4. የወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ቦርድ ስልጣንና ተግባር ዝርዝር፣

1. በክልሉ እና በዞኑ/ከተማ አስተዳደሩ ኢንቨስትመንት ቦርድ ውሳኔ መሰረት ተግባራትን ይፈጽማል፡፡
2. በወረዳው ውስጥ የሚቀርቡ የኢንቨስትመንት ጥያቄዎችን አስፈላጊነታቸውን፣ የተጠየቁት የኢንቨስትመንት አማራጮች ለአካባቢው እና ከአካባቢው ፍላጎት ጋር የሚጣጣም መሆኑን በመለየት እና በማወዳደር የተሻሉ ብሎ ያመነባቸውን ከውሳኔ አስተያየት ጋር ጉዳዩ ለሚመለከታቸው መምሪያዎች ይልካል፡፡
3. ሌሎች በክልሉ እና በዞኑ ኢንቨስትመንት ቦርድ የሚሰጡትን ተግባራት ይፈጽማል፡፡

## 7. አቤቱታ የማቅረብ መብት፣

### 7.1. አቤቱታ የማቅረብ መብት እና አቤቱታ የሚቀርብበት ውሳኔ፣

1. ማንኛውም ባለሃብት ከኢንቨስትመንቱ እና ኢንዱስትሪ ልማት ጋር የተያያዘ ቅሬታ ካለው መንግስታዊ መዋቅሩን ጠብቆ አግባብ ላለው አካል አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው::
2. ኢንቨስትመንትን አስመልክቶ በተሰጠ የመጨረሻ የአስተዳደር ውሳኔ ላይ በባለሃብት የሚቀርብ አቤቱታ፣ ቀልጣፋ፣ ሚዛናዊ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ይፈታል::
3. ይህ ስርዓት ኢንቨስትመንት ላይ ለመሰማራት በቀረበ ጥያቄ ላይ አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ለሚቀርብ አቤቱታም ተፈጻሚ ይሆናል::

### 7.2. የአቤቱታ አቀራረብ ስነ-ሥርዓት፣

1. ማንኛውም ባለሃብት/ኢንቨስተር በቢሮው የሚተላለፍ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔን በመቃወም ለቦርዱ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል::
2. ቢሮው ውሳኔው ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ በሰባት (፯) የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታ ላቀረበው አካል ወይም ለባለሀብቱ የጽሑፍ ቅጂ ይሰጠዋል::
3. በቢሮው በተሰጠ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለቦርዱ የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ ባለሀብቱ ውሳኔው መሰጠቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ20 (ሀያ) የሥራ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት::
4. ቦርዱ በቀረበለት አቤቱታ ላይ አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል::

## 8. የቦርዱ ውሳኔዎች ተደራሽነት፣

1. ቦርዱ የሚወስናቸው ውሳኔዎች ወዲያውኑ ተፈጻሚ የሚሆኑ ሲሆን ውሳኔዎቹ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለሚመለከታቸው ቢሮዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል::
2. የቦርዱ ውሳኔ የደረሰው ቢሮ ሌላ አሳማኝ ምክንያት ካልቀረበ በስተቀር በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው በውሳኔው መሰረት ተፈጻሚ ማድረግ አለበት::

## 9. የቦርዱ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር፣

1. የቦርዱ ሰብሳቢ ቦርድ አባላትን የማዋቀር እና በማንኛውም ወቅት ለአስቸኳይ ስብሰባ ወይምሥራ የመጥራት፤

2. እንደ አስፈላጊነቱ እና በሌሎች ህጎች የተወሰኑት እንደተጠበቁ ሆነው የቦርዱን አባላት ውክልና በመስጠት በቦርዱ መከናወን ያለባቸውን ተግባራት ለይቶ የማሠራት፤
3. ሌሎች ለቦርዱ ስራ አፈጻጸም ተገቢ የሆነ ስራ የመስራት ሙሉ ስልጣን ይኖረዋል።

## 10. የቦርዱ ውሳኔና የሥብሠባ ሥነ-ሥርዓት፣

1. ቦርዱ በየወሩ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤
2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የቦርዱ አባላት በማንኛውም ስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፤
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በተቻለ መጠን በስምምነት እና በአሳማኝ ሁኔታ በሙሉ ድምጽ ይወሰናሉ፤ ስምምነት ላይ የማይደረስባቸው ሁኔታዎች ሲኖሩ በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም፣ የተሰጠው ድምጽ እኩል ድምጽ ከያዘ ሰብሳቢው የሚደግፈው የውሳኔ ሀሳብ የመጨረሻ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች፣

## 11. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን፣

ቦርዱ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስችሉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

## 12. ደንቡን ስለማሻሻል ፣

ቦርዱ ደንቡን ማሻሻል አስፈላጊነው ብሎ ሲያምን ለመስተዳድር ምክር ቤት ሀሳቡን ማቅረብ ይችላል። ይኸ እንደተጠበቀ ሆኖ መስተዳደር ምክር ቤቱም የቦርዱን ሀሳብ መነሻ በማድረግ ወይም በራሱ አነሳሽነት ደንቡን ማሻሻል ስልጣን አለው።

## 13. የሽግግር ድንጋጌዎች፤

1. ይህ ቦርድ ከመቋቋሙ በፊት በክልል መስተዳድር ምክር ቤትም ይሁን በቢሮዎች ወይም በሌሎች ኮሚቴዎች ይታዩ የነበሩ አሁን በዚህ ደንብ ለዚህ ቦርድ ስልጣንና ተግባር የተሰጡ ጉዳዮች፣ እና ቀርበው በመታየት ላይ ያሉ ተያያዥ ጉዳዮች በሙሉ በዚህ ደንብ መሰረት በተቋቋመው ቦርድ የሚታዩ ይሆናል፡፡
2. ከዚህ ቦርድ ስልጣንና ተግባር ውስጥ ያልተካተቱ የኢንቨስትመንት የማስፋፊያ እና የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እንዲሁም መሰል ሌሎች የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች ጉዳዩ በሚመለከታቸው ቢሮዎች ውሳኔ የሚሰጥባቸው ይሆናል፡፡

## 14. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች፣

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 15. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ፣

ይህ ደንብ በክልል መስተዳድር ምክር ቤት ጸድቆ እና በርዕሰ መስተዳድር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ባህር ዳር ነሀሴ 2014 ዓ/ም**

**ይልቃል ከፋለ (ዶ/ር)**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት**

**ርዕሰ-መስተዳድር**



